ዴሞክራሲያ

# ኢሕአፓ-- ሚያዝያ 1964-ሚያዝያ 2001

## ቀጣይ ትግል- ፅኑ ትግል- ክቡር ቃል ኪዳን

*ዴሞ ልዩ ዕትም* *ሚያዝያ 2001 ዓ.ም*

ታሪክ ይፍረድ፣ ትውልድ ይናገር ከተባለ መሬት ለአራሹ፣ መብት ለሠርቶ አደሩ ብሎ ለዓመታት ሲታገል ከነበረው እንቅስቃሴ የተወለደ ድርጅት ነው ኢሕአፓ:: ኢሕአፓ ከተመሰረተበት ከሚያዚያ 1964 ዓ.ም ጀምሮ ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወገንተኛነቱንና ሀገር ወዳድነቱን በይፋ አውጆ የጠላት ጥንካሬ ሳያስበረግገው፣ የትግሉ መራራነት ሳያዳክመው፣ ውድ ሕይወትን በመስዋዕትነት ማቅረብ ሳያሸማቅቀው እስካሁን ድረስ የታገለ፣ አሁንም እየታገለ ያለ ድርጅት መሆኑን በተግባር ያስመሰከረና አሁንም እያስመሰከረ ያለ አንጋፋ ድርጅት ነው::

በርግጥም ኢሕአፓ ያደረጋቸውን ተጋድሎዎች በትኩረት ላጤናቸው ከዛሬ 37 ዓመት በፊት የነበረው የፖለቲካ፥ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ የግዴታ ይህንን ድርጅት በአንጋፋነት አምጦ መውለድ ነበረበት የሚለውን አባባል፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክ በቅርበት የሚከታተሉ በርካታ የፖለቲካ ሊቃውንትና የሥነ ምግባር ተመራማሪዎች የሚስማሙበት ነው:: ከሕዝቡ አብራክ ተወልዶ ከሕዝቡ ጋር እየተጓዘ፣ የሕዝቡን ኑሮ እየኖረ የታገለ ኃይል ነው:: መከታውንም ይህንኑ ሕዝብ ያደረገው ኢሕአፓ፥ በሕዝብ ኃያልነትና አቸናፊነት በመተማመን ያደረገውን ትግልና በትግሉ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያሳረፈውን አሻራ ማንም ሊፍቀውም ሆነ ሊሰርዘው የማይችል ሐቅ ነው:: በዚሁ አኩሪ ተግባሩ፣ ለሕዝቡ ባለው ቅንነቱና ታማኝነቱ፣ ለችግርና ለመከራ በአይበገሬነቱ ጥቅማችንን ይቃረናል ብለው ያመኑና በግንባር ቀደምትነት ትግሉን አምርረው የሚጠሉት ክፍሎች ያልሸረቡበት ሴራ ያላደረጉበት ጦርነት አልነበረም:: ይሁንናም ጠላቶቹ ምን ያህል ህልውናውን ሊያጠፉ ቢራኮቱ፣ ጣሪኩን ጥላሸት ለመቀባት ቢጥሩ፣ ምን ያህል መሪዎቹን፥ አባላቱንና ደጋፊዎቹን ደብዛቸውን ለማጥፋት ቢታክቱ ኢሕአፓን ከሕዝብ ልቦና ሊፍቁት አልተቻላቸውም:: እንዲያውም ዓመት በዓመት እየተተካ በሄደ ቁጥር እየጎለበተ፣ በሂደት የተሰሩ ስህተቶችን እያረመ፣ በደም የተገነቡ

ተመክሮዎችን በማንገብ፣ የኢትዮጵያን ሁናቴን ከዓለም አቀፉ ሁኔታ ጋር እያዛመደ ትግሉን ቀጥሎ ተገኘ እንጂ አልተበገረላቸውም። ነቀርሳዎች አይጠፉምና ድርጅቱን ከውስጥ ሰልበው ከአገዛዙ ጫማ ሥር ለማንጠፍ የጣሩትንም አሳፍሮ፥ ሃሳባቸውንም ከውስጡ ጠራርጎ ጥሎ፣ ሕጋዊ አመራሩንም በዴሞክራሲያዊ ሁኔታ መርጦ ውህደቱን በመጠበቅ፣ ለትግል በትግል ተፈትኖ ነጥሮ የወጣ ድርጅት ነው። ለቅጥረኝነት ሊዳርጉት የጣሩትን በቆራጥነት እምቢኝ እሻፈረኝ በማለት አሳፎሮ፥ ቅሌት አከናንቦ በመጡበት ሸኝቷቸዋል። በዚህም የህዝብ አለኝታነቱን በተግባር አረጋግጦ የግሉን አስተዋጽዖ ለማበርከትና ግዳጁን ለመወጣት በትግል ላይ ይገኛል።

በዚህ የትግል ውጣ ውረድ ውስጥ በርካታ ተመክሮዎችን ያካበተ በመሆኑ፣ የሥልጣን ጥመኛ የሆኑ ቡድኖች ከሚያቀርቡት መግለጫና ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ለማድረግ ያቀዱትን ጭምር አስቀድሞ ለመተንበይና ብሎም ሕዝብ እንዲገነዘባቸውና ነቅቶም እንዲከላከላቸው ለማድረግ ያስቻለው መሆኑን በተለያዩ ጊዜያት አረጋግጧል። ወያኔ ከውልደቱ ጀምሮ በትግራይ ይንቀሳቀስ በነበረበት ወቅት ይከተለው የነበረው ፖሊሲ የተሳሳተና ሥልጣን ሊጨብጥ ከቻለም በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ምን ያህል ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ግልፅ እንዲሆን ያደረገው ተጋድሎ፣ በዚህም የመለስ አገዛዝ ፓርቲው የታገለላቸውን መፈክሮች እንዳሉ ወደጎን በማረግ እንዳሻው ሊፈነጭ፣ ሕዝቡን ሊያወናበድ አለመቻሉ የዚሁ ውጤት መሆኑ በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችል ነው። ስለፌደራሊዝም ሥርዓት፥ ስለምርጫ ትርጉምና ይዘት፥ ስለሕገመንግሥት፥ ስለሥልጣን ክፍፍል፥ ስለመድበለ ፓርቲና ስለዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት፥ ስለሕግ የበላይነት፥ ስለነፃ ፕሬስ፥ ስለሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት፥ ስለሕዝብ የሥልጣን ምንጭነት፥ ስለትግል ምንነት ያቀረባቸው ትንተናዎች በሕዝብ ሕሊና ውስጥ ተቀባይነትን ያገኙ በመሆናቸው፣ የሕዝቡ አለንጋዎች ሆነው ወያኔን እየለበለቡ ናቸው። በዕውነትም ኢሕአፓ የትግል ዩኒቨርሲቲ ነው ቢባል ሀቁን ማቅረብ ነው የሚሆነው።

በአሁኑ ወቅት ለኢሕአፓ ልዩ ትርጉምና የማንነቴ መግለጫ ነው ብሎ የሚመለከተውን ወርሀ የካቲት ስናስታውስ በ66 በዚህ ወር በተደረገው ሕዝብዊ እንቅስቃሴ፣ ሀገር ወዳድ ታጋዩ ኃይል በጊዜው በነበረው አቅም ሊያስወግዳቸው የታገላቸው ችግሮችና ቀውሶች ዛሬም ከሞላ ጎደል የኢትዮጵያን ሕብረተሰብ የሚያመሰቃቅሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። በመሆኑም ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ፣ ሕዝብ ይህን ያህል መስዋዕት ከፍሎ ባለበት፣ ለምንስ መፍትሄ እንዳላገኙ መቃኘቱ አስፈላጊነቱ የማይታበል ነው። ስለሆነም ከተጨባጩ ሁኔታ በመነሳት ሥርዓቱን ለመለወጥ ይቻል ዘንድ ይበጃል ያላቸውን በራዕዮቹ፥ በምኞቶቹና በፍላጎቶቹ የተመሰረቱ የመቀስቀሻ፥ የማደራጃና የማታገያ መፈክሮቹን ወደኋላ መለስ ብሎ በአዲስ መገምገሙና ማጤኑ የነገ ግዳጅን ለመወጣት ይበልጥ ግልፅ ያረጋል ብሎ ያምናል ኢሕአፓ። በመሆኑም አጠቃላይ በሆኑ የሀገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ ጥልቀት ላይ ሳናተኩር አብይ የሆኑትን ጥያቄዎች ዳግም መዳሰሱ ጥራት ሰጪ ነውና እነሆ እንላለን።

- በቅድሚያ በአርሶ አደሩ ሁኔታ ላይ ብንጀምር፤
  - የፊውዳሉ ሥርዓት ብዙኃኑን ገበሬ ወይም አርሶ አደር በጢሰኝነት ይዞ እያስገበረ ሲያሰቃይና ሲበዘብዝ የነበረ በመሆኑ "መሬት ለአራሹ!" ይሁን በሚለው መፈክር ሥር አጥብቆ ታግሏል፡፡ በተለያዩ የወቅቱ መግለጫዎቹ ግልፅ እንዳደረገው፥ መሬት ለአራሹ ሲባል መሠረታዊ ይዘቱ አርሶ አደሩን ከብዝበዛ ማላቀቅ፥ በሚያርሰው መሬት ላይ ብቻ ሳይሆን በሚያመርተው ምርትና ግላዊ ንብረቱ ጭምር ለመወሰን ባለ ሙሉ መብት ለማድረግ፤ ከዚህ ባሻገር ደግሞ በሀገሩም ሆነ በራሱ የወደፊት እጣ ላይ እንደሌሎቹ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሁሉ ተገቢ ድርሻውን እንዲያበረክት የማስቻል ይዘትን ያቀፈ ነበር፡፡ መሬት ለአራሹ፤ መብት ለጭቁኑ ብሔረሰብ ከሚለው መፈክር ጋር አያይዞ ለዴሞክራሲ የታገለው ሁለቱም ጥያቄዎች በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ የተቆላለፉ ስለነበሩ፤ እንዲሁም ሀገር የጋራ ናት የሚለውን መሠረተ ሃሳብ ሕይወትና እስትንፋስ ያገኝ ዘንድ እኩልነት በፖለቲካውና በኤኮኖሚው መስክም መረጋገጡ ወሳኝ መሆኑን በማመን ነው፡፡
  - ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነቱ፥ ለመብቱ፥ ለዕኩልነቱ፥ ለሀገሩ መከበር ያልተቋረጠ ትግል ቢያደርግም በየጊዜው የተቀያየሩና በጨቋኝነታቸው፤ በመብት ረጋጭነታቸው የተመሳሰሉ አገዛዞች በጠመንጃ ኃይል ሥልጣን ይዘው ግቡ እንዳይሳካ አድርገውት ቆይተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ይህ የሰፊውን አርሶ አደር ፍላጎትና ጥቅም ያንፀባረቀና ከፍተኛ መስዋዕት የጠየቀ ጥያቄ፤ እስካሁን ድረስ ተገቢ ምላሽ ባለማግኘቱ፤ ከሁኔታው ጋር የተጣጣመ ትግል ማካሄዱ የግድ እያለ ይገኛል፡፡ በሕዝቡ ግፊትና እንቅስቃሴውን ለመግታትና ሕዝብን ለማደናገር ደርግ ያወጀው የመሬት አዋጅ በርግጥም በባላባቱና በጭሰኛው መካከል የነበረውን የጌታና የሎሌ ግንኙነት ሊያስወግድ ቢችልም ገበሬውን ነፃነቱን ሊያጎናፅፈው፤ የሚያርሰው መሬት ባለቤት ሊያረገው አልቻለም፡፡ እንዲያውም ይመራበት በነበረው ፖሊሲ መሬትን በሕዝብ ሳይሆን በአገዛዙ ቁጥጥር ሥር በማድረግ ገበሬውን የሱ ጥገኛ አደረገ እንጂ ይህ ነው የሚባል የኑሮ መሻሻል አላስገኘለትም፡፡ ስለሆነም ከነበረበት የድህነት አረንቋ፤ ከበሽታና ከችግር አልተላቀቀም፡፡ ይህንን ችግሩን ተቋቁሞ ደርግን ለመጣል በተደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል የራሱን አስተዋፅዖ ቢያበረክትም ዛሬም ከድጡ ወደማጡ ሆኖበታል፡፡ በወያኔ አገዛዝም አርሶ አደሩ የመደብ አንድነቱ እንዲፋለስና በብሔር ብቻ ተወስኖ እንዲታጠር፤ በክልል እንዲከፋፈል ተፈርዶበት በአዲስ ሁኔታ እንዲበዘበዝ ሲደረግ፤ ሰላምና ማህበራዊ መረጋጋት ርቆበት በተዛባ የመሬት ፖሊሲ የተነሳም ዛሬም በግልፅ የወያኔ ጭሰኛ ሆኖ ግፍን እየተጋተ፥ ፍዳውን እያየ ይገኛል፡፡ በነፃ ተደራጅቶ ጥቅሙንና ፍላጎቱን ለማስከበር አልተቻለውም፡፡ ሊከፍለው በማይችለው የማዳበሪያ ዋጋ የተነሳም ከመሬቱ ይፈናቀላል፡፡ በዚህም የተነሳ ለማረስ የሚገለግልባቸውን በሬዎቹን እንዲሸጥ ተገዶ ከነቤተሰቡ ለረሀብና ለሥራ አጥነት ይዳረጋል፡፡ እንደቀደሙት ሁሉ አሁንም በአዲሶቹ አገዛዝ አባላት መበዝበዙ ቀጥሏል፡፡ በቂ ጥናት ባልተደረገበት የጥቂቶችን

በጫንቃው ላይ የተፈናጠጡ ክፍሎችን ፍላጎት ለማሟላት ሲባል፥ ለም በሆነ የእርሻ መሬቱም ሆነ በሚኖርበት አካባቢ የሚገኙ ወንዞችና ሐይቆች በኬሚካል እየተበከሉ፥ እየተበላሹ ይገኛሉ። የመሬቱ ባለቤት የመለስ አገዛዝ በመሆኑ ገበሬው በወያኔ ቢሮክራሲ ከፍተኛ መጉላላት የሚደርስበት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ መንግሥታዊ የሆኑ ማናቸውንም አገልግሎቶች ተቋዳሽ ለመሆን ሕጋዊ መብቶቹን ለማስከበር እንዳይንቀሳቀስ በአገዛዙ ታፍኗል። የአካባቢውን የተፈጥሮ ሚዛ ለመጠበቅና የአየር ብክለትን ለመከላከል አልተቻለውም። እንዲያውም በየጊዜው ለአስከፊ የምግብ እጥረት እርዳታ መለመኛ አሃዝ ማሟያነት ተዳርጓል። በመሆኑም መሬት ለገበሬው/አርሶ አደሩ ዋነኛውና መሠረታዊ የኑሮው ወይንም የገቢ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካና የኤኮኖሚ ጥያቄ ነውና ዛሬም ገበሬውን የመሬት ባለቤት ለማድረግና በነፃ የመደራጀት መብቱ እንዲከበር መታገል አቢይ ተልዕኮ ሆኖ ይገኛል።

- የዴሞክራሲ አካል የሆነውን የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄን ስንመለከትም፣
  - የብሔረሰቦች እኩልነት እንዲረጋገጥ፣ ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ያላቸውን መብት ለማስከበርም ፓርቲው በስፋት የተንቀሳቀሰበት አቢይ ተልዕኮ ነው የነበረው። ኢሕአፓ የብሔረሰቦችን ዕኩልነትንና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን፥ ራስን በራስ የማስተዳደር መብትን ሲቀበል የሀገር አንድነትም በዚሁ ይረጋገጣል ሲል፣ የመገንጠል በርን መክፈት ነው በማለት የተቃወሙትን ክፍሎች የስህተት ጎዳናቸውን እንዲያስተካክሉ ባደረገው ተጋድሎ የሕይወት ግብር ከፍሎበታል። ከተለያየ አቅጣጫ ይስተጋቡ የነበረቱንና ለአንድነት ጠንቅ የሆኑትን ሁለት ፅንፈኛ የሆኑ አስተሳሰቦችን - ትምክህተኝነትንና ጠባብ ብሔረተኝነትን - ቢታገልም፣ በአንድ በኩል በዕኩልነት መጥፋት በሌላ በኩል ጠባብ ብሔረተኞች ባካሄዱት የጥላቻ ዘመቻ ጉዳዩ መፍትሄ ሳያገኝ ቆይቷል። በወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ ከፋፋይ ፖለቲካ የተነሳ ችግሩ ይበልጥ እንዲባባስ መደረጉ በጥያቄው ላይ ኢሕአፓ ትኩረት ሰጥቶ እንዲንቀሳቀስ አድርጎታል። ስለዚህም የመንግሥት ቅርፅ ጥያቄ ለብሔረሰብ ጥያቄ ከምንሰጠው መልስ ጋር የተያያዘ መሆኑን ከግንዛቤ ማስገባቱ አስፈላጊ ነው። ይህንን ስንወስድ የሕዝብ መብትን የሚያረጋግጠውና ሥልጣንን ለሕዝብ የሚያጎናፅፈው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዕውን ሳይሆን ድፍን ባለ አንድነት ዕውን ሊሆን አይችልም የሚለው ሐቅም መጨበጥ ይኖርበታል። ይህን ሐቅ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በብሔረሰብ ደረጃ እየነጣጠለ የሚገኘውን የወያኔ ፖለቲካ በማስወገድ የሀገር አንድነት በዴሞክራሲና በዕኩልነት ላይ ተመሥርቶ ዕውን የሚሆንበትንና ሕዝብም የወደፊት ትኩረቱን በጋራ ለጋራ ብልፅግና ሊያውል የሚችልበትን የፌደራል መስተዳደርን በአማራጭ አቅርቧል። ከዚህ ጋር ተያይዞም የሁኔታውን ልዩነት በማጤን በኤርትራና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል ያሉትን ታሪካዊና ባህላዊ ትስስሮችን በማየት፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለዘላቂ ሰላም፣ እድገትና

ብልጽግና ይበጃል ያለውን ፌደራላዊ የመፍትሄ አማራጭ ለኤርትራ ተገቢና የሚያዋጣ ነው ብሎ ማቅረቡ ይታወሳል፡፡

- በተለያዩ መግለጫዎች እንደተገለጸው "ኢሕአፓ የብሔር ጭቆና ይወገድ የዕኩልነት መብታቸው ይከበር በማለት ቀዳሚ ቢሆንም ጠባብ ብሔረተኞች ሀገር ለመገነጣጠል በሕዝብ መሃል ጥላቻን ለመፍጠር የኢትዮጵያን ታሪክ በርዘው" በመቶ ዓመት ገድበው "ሕልውናዋን ለመሰረዝ ሲሞክሩ አጥብቆ በመቃወሙና በመታገሉ ከወያኔ እስከ ሻዕቢያ፥ ከኦነግ እስከ ምሶነአግ በጠላትነት መድበው ተዋግተውታል፤ ታግለውታል፡፡ ሊያጠፉት ሊያዳክሙት ጥረዋል፡፡" ወያኔ ገና ከውልደቱ ኢሕአፓን ለማጥፋት የጣረ ብቻም ሳይሆን ሥልጣንም ከጨበጠ በኋላም በዚሁ ጥላቻው ቀጥሎበት ይገኛል፡፡ በመሆኑም በኢሕአፓና በወያኔ መካከል ያለው ቅራኔ መሠረታዊ በመሆኑ ሊፈታ የሚችለው የወያኔ አምባገነናዊ ሥርዓት ተወግዶ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲተካ ብቻ ነው የሚለው የማታገያ መፈክር አሁንም የጸና ነው፡፡ የብሔረሰብ ጥያቄ የሚፈታው በዴሞክራሲ መስፈን በመሆኑ የወያኔ አገዛዝ በቅድሚያ መወገዱ አማራጭ የሌለው ነው የሚለው እቋሙን አስረግጦ ይቀጥልበታል፡፡

- ትኩረታችንን ወደሠርቶ አደሩ ስናነጣጥርም፤

የሠርቶ አደሩ መብት ይጠበቅ እንላለን፡፡ ላብ አደሩ ላቡን አንጠፍጥፎ የሚያመርተው ምርት ተጠቃሚ እንዲሆን ከብዝበዛ፥ ከውርደት ከስቃይ ነፃ ይሁን፡፡ መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር በነፃ የመደራጀት መብቱ ይከበር፤ በድርጅቱ የውስጥ ጉዳይ መንግሥት ጣልቃ አይግባበት፤ ከአሠሪው ጋር ለመደራደር የሥራ ማቆም አድማና ጥያቄውን በሰላማዊ ሰልፍ ጭምር ለማቅረብ መብቱ ይከበርለት፤ በመንግሥትም ሆነ በአሠሪው ለጥቃት አይጋለጥ፤ ልቅ በሆነ የነፃ ገበያ የኤኮኖሚ ሥርዓት እንዳይበዘበዝ የኤኮኖሚ ዋስትና ይበጅለት፤...በተሰኙት መፈክሮች ሥር ላብ አደሩን አደራጅቶና ቀስቅሶ ታግሎ አታግሏል፡፡ የድርጅታቸው ነፃነት እንዲጠበቅ፤ መሪዎቻቸውን በነፃ እንዲመርጡ፤ ተለጣፊ ድርጅት እንዳይመሠረትባቸው የሚሉት አሁንም አቢይነት ያላቸው ጥያቄዎች በመሆናቸው ይታገልላቸዋል፡፡ በሕዝባችን ላይ ተቆናጠው ላብ አደሩን ላቡን፥ ደሙንና ሥጋውን ሙልጭ አርገው አንጠፍጥፈው ሊበዘብዙት የሚመኙትን የሥልጣን ጥመኞች አጥብቆ ታግሏል አሁንም በዚህ ይቀጥልበታል፡፡ ላብ አደሩ በነፃ ማኅበር የመደራጀት መብት ተነፍጎት ለጭፍን ብዝበዛ ተዳርጎ በኑሮ ውድነትና በአገዛዙ ጭካኔ እየተሰቃየ ባለበት ኢሕአፓ ከላብ አደሩ ጎን በመሆን ችግሩ የሚቃለበትን ዘዴ (መፍትሄውን) አብሮ ያፈላልጋል፡፡ የትግል አንድነትም በዚሁ ይገለጻልና ለላብ አደሩ መብት የሚታገሉ መሪዎቹ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ይደግፋል፡፡ ለተግባራዊነቱም ይንቀሳቀሳል፡፡

- *የዴሞክራሲን ሁናቴ የወደፊቱን ለማመላከት ያለፈውን ጠጋ ብለን ስንቃኝም፤*
  - *ኢሕአፓ ስለዴሞክራሲ ያለውን ግንዛቤ "ዴሞክራሲ ሲሉ ዴሞክራሲ ስንል" በሚል በልሳኑ በዴሞክራሲያ፥ በመልክዕክተ ኢሕአፓ፥ በፍኖተ ዴሞክራሲ የሬዲዮ ስርጭቱና በፍካሬ እንዲሁም በተለያዩ መጽሔቶቹ፥ በበራሪ መግለጫዎቹ ጭምር በተለያዩ ጊዜያትና በተደጋጋሚ ግልፅ በሆነ መልኩ በዝርዝር አቅርቧል:: በቅርቡም "ኢትዮጵያ - ዴሞክራሲዊ አማራጭ - ችግሮቿና የወደፊት እጣዋ" በሚል በእንግሊዝኛ በድጋሚ ባሰራጨው ጽሑፉ ላይ በሚገባ አብራርቷል::*
  - *ስለሆነም ዴሞክራሲ እንደፖለቲካ አስተሳሰብና አሠራር፤ እንደመንግሥት ቅርጽና የአስተዳደር ዘይቤ፤ ለተናጠልም ሆነ ለጋራ ዕኩልነት፥ ነፃ መሆን፤ በደስታ መኖር፤ ያለምንም ተጽዕኖ መናገር፥ መጻፍ መደራጀት፥ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር መብት መረጋገጥ፤ ማንም ዜጋ በሕግ ፊት ዕኩል መሆን፤ የሕዝብ ልዕልና መከበር ...ወዘተ የሚሉት መሰረታዊ የዴሞክራሲ አስተሳሰቦችን ይዘት ያገናዘበ ሊሆን ይገባል:: እናም እነዚህን ይዘታቸውን አገናዝበን ከወሰድን በርግጥም በሀገራችን ያለፉትን* 37 *በተለይም የወያኔን* 18-*ኡን ዓመታት ስናጤን ዴሞክራሲ በሀገራችን እንዲመሰረት ገና እልህ አስጨራሽ ትግል የሚያስፈልግ መሆኑ ከግልጽም ግልጽ ነው::*
  - *የሕዝብ ልዕልና ደብዛው ተፈልጎ የሚገኝ አልሆነም:: የሥልጣን ባለቤት ሕዝብ ሳይሆን ኢሕአፓ በዴሞክራሲ ልዩ እትም እንደገለጸው ኢትዮጵያን ሊያጠፉ ጊዜ ባጠረው "በመሠረቱ ውልደታቸው ከትግራይ የሆኑ የድርጅት መሪዎችና ካድሬዎችን ባቀፈ፤ ተለጣፊዎችን በአጃቢነት በኮለኮለ ...ሕብረተሰባዊ መሠረቱ በጠበበ፤ የፖለቲካ ራዕዩ ጠባብ ብሔርተኝነት በሆነ፤ በፖለቲካ ሥልጣኑ ተመክቶ የፖለቲካ ጡንቻውን ባደለበ፤ በጦርና በአፈና ኃይሉ ተማምኖ በሚገዛ ፀረ ሕዝብ ገዢ መደብ" በመለስ ዜናዊ ቁንጮነት በተሰየመ አገዛዝ ሥር የሚገኝ ነው:: የሕግን የበላይነት ሕገ መንግሥቴ በሚለው ቢደረድርም፥ የአገዛዙ ባለሥልጣናት ግን ከሕግ በላይ ናቸው:: ነፃ የዳኝነት ሥርዓት ባለመኖሩ የአገዛዙ ጠባዮች የሆኑት መብት ረገጣ፥ አድልዎና ሙስና ከምንጊዜውም በላይ ተስፋፍተዋል:: የህዝቡ በንግግርና በፅሑፍ ተቃውሞን የማሰማት፤ ሰላማዊ ሰልፍ ሆነ የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ መብቶች፤ ሀገሪቷ በክልል በመሸንሸኗ የመኖሪያ ቦታን የመምረጥና የመለወጥ ሁኔታ ከፍተኛ ጋሬጣ ተደቅኖባቸውል:: በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የአገዛዙ ተቃዋሚዎች በተለያዩ እሥር ቤቶች በመታጎር ይሰቃያሉ:: ሥየልና ግፍ በታሰሩ ዜጎች ላይ መፈጸም የተለመደ ተግባር ነው:: ደብዛቸው እንዲጠፋ የተደረጉ ዜጎቻችን፥ የኢሕአፓ አባላትን ጨምሮ፥ በርካታ ናቸው:: የሃይማኖት ዕኩልነት ተረጋግጧል፤ በዕምነት መካከል የነበረው ልዩነት ተወግዷል ቢባልም በአገዛዙ ካድሬዎች በሚጠነሰስ ሴራ የሚከሰቱ ፍጅቶች በርካታ ናቸው፤ በዚህ የተነሳም ማኅበራዊ መረጋጋት ማግኘት አልተቻለም:: የጾታ ዕኩልነት ከወረቀት ያለፈ አይደለም:: አርሶ አደሩና ሠራተኛው፥ ተማሪውና አስተማሪው፥ ነጋዴው፥*

ሴቶች ባጠቃላይ የሕብረተሰቡ አባላት በአገዛዙ መብቶቻቸው በመታፈናቸው የተነሳ ከወያኔ ጋር ተቃርነውና ተፋጠው ይገኛሉ። በመልካም አስተዳደር እጦት የሕግ የበላይነት አለመኖር፣ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት አለመከበር፣ በነፃ የመደራጀት፣ ጥቅምንና ፍላጎትን በነፃ የማስተጋባት አለመኖር፣ እነዚህ ሁሉ ገና ምላሽን ጠያቂ ናቸው። በመሆኑም ዴሞክራሲ ያለገደብ ይከበር የሚለው አሁንም መሪ መፈክራችን ሆኖ ይገኛል።

- የሀገር አንድነት በሕዝብ ዕኩልነት ባለመረጋገጡ ሕዝቡ በክልልና በቋንቋ በሃይማኖትና በሌላም እንዲከፋፈል እየተደረገ ለግንጠላና ለላቀ የእርስ በርስ ግጭት እየተገፋና እየተቀሰቀሰ፣ ከፍተኛ የሕዝብ ሕይወትን ያስከፈሉ ግጭቶችንም አስከትሏል። አንቀጽ 39 ሀገሪቱን የሚበታትን መሆኑ በገቢር የተረጋገጠ ቢሆንም አሁንም ይህንን አንግበው ለግንጠላ ሊጠቀሙበት የሚጥሩ ተገንጣይ ቡድኖች በመኖራቸው አጥብቆ መታገሉ ዛሬም ወቅታዊ ነው።

- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ሉዓላዊነት፥ ነፃነትና ክብር ይጠበቅ የሚለው ዛሬ ከምንግዜውም በላይ አንገብጋቢ ሆኖ ይገኛል። በምዕራቡ ወሰናችን ለሱዳኑ የተሰጠው መሬት፣ የሱዳን ጦር በቦታው መስፈር፣ ነዋሪው ሕዝብ ከቀዬው እንዲባረር መደረጉና በሁለቱም የጦር ኃይል መዋከቡ፥ መታሰሩ ይህንን መፈክር ዛሬም ማስተጋባቱ ወሳኝ ያደርገዋል። ኢሕአፓ ዛሬም እንደትላንቱ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፥ ክብርና አንድነት ይታገላል። የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚጻረሩ የቅርብና የሩቅ ባዕዳን ኃይሎችን ይቃወማል። ከኢትዮጵያም እንዲወጡ ይቀሰቅሳል። ኢትዮጵያ የባዕዳንን አጀንዳ ማስፈጸሚ ይቁም፣ ብሐራዊ ክብሯም ይጠበቅ እያለ ኢሕአፓ አለማሰለስ መታገሉን ይቀጥላል። ብሔራዊ ክብሯም እንዲጠበቅ ይታገላል።

- ለውጥ በዴሞክራሲያዊ የሽግግር መንግሥት ሂደትን ጥያቄን አስመልክቶም፣
  - አንድን አምባገነን መንግሥት አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የግዴታ የሽግግር ሂደት ማስፈልጉ ግልፅ ሆኗል። ሀገራችን ይህ የሽግግር ሂደት እንደሚይስፈልጋት ያለፈው ሕዝቡ የታገለለት ዓላማ ሳይሳካ መቅረቱ ይህንኑ የሚያመልክት ነው። በየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ታጋዩ ኃይል የጃንሆይን ባላባታዊ አገዛዝ ቢገረስስም ኢሕአፓ በወቅቱ የሽግግር አስፈላጊነትን በመግለፅ ቀዳሚ ሚና መጫወቱ የሚዘነጋ አይደለም። በተግባርም ኢሕአፓ ይህን ዋና ጉዳዩ አድርጎ የሽግግር ሂደት ዕውን ይሆን ዘንድ የጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት መቋቋምን ጥያቄ በማንሳት ቢታገልም በደርግና ከሱ ጋር በተቆራኙ በወቅቱ ባንዳ ምሁራን ተብለው በሚጠሩ ቡድኖች ተጨናገፈ። ይህ ጥሪ ለዴሞክራሲ መመሥረት ጥርጊያ መንገድና ለሽግግር መልካም ዕድል ሆኖ ሳለ በመጥፎ በመተርጎም የራሳቸውን ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝ ለመመሥረት ተሯሯጡ። እነዚያን በሰላማዊ መንገድ ይህ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም የጠየቁትንና የታገሉትን ኢሕአፓዎችና ሀገር ወዳዶች

ባሰቃቂና ባሳዛኝ ሁኔታ ጨፈጨፏቸው:: የጥሪውን መሠረታዊነት ግን የ17-ኡ ዓመት አገዛዛቸው አጉልቶ አሳየ እንጂ አልቀነሰውም::

- o የደርግ ወታደራዊ አገዛዝ መውደቂያው በተቃረበ ወቅትም ኢሕአፓ እንደገና ሰፊ መሠረት ያለው ሁሉንም የአንድነትና የዕኩልነት ኃይል የፖለቲካና ሕዝባዊ ድርጅቶችን ያቀፈ፣ ዝርዝር ተግባሩና የሥልጣን ዘመኑ በግልፅ የተቀመጠ የሽግግር መንግሥት ቢያቀርብም በደርግና በወያኔ የጋራ እንቅፋትነት ዳግም ሊጨናገፍ ቻለ:: ዛሬ ደግሞ ይኸው ጥያቄ ከምንጊዜውም በላይ አንገብጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ሕዝባችን ለደረሰበት የፖለቲካ፥ የማኅበራዊና የኤኮኖሚ ቀውስ ተጠያቂ የሆነው የወያኔ አገዛዝ በሚደረገው የሕዝቡ ትግል ተወግዶ ዘላቂ ሰላምና ማኅበራዊ መረጋጋት የሰፈነበት መንግሥት መመሥረት እንዲቻል ኢሕአፓ በሽግግር ሂደት የማለፉን አስፈላጊነት ጥሪ በድጋሚ አቅርቧል:: በቅርቡ ሃሳቡን በዝርዝርና በጽሑፍ በማቅረብ ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ እያካሄደበት ይገኛል:: ካለፉት ሁኔታዎች ተመክሮ በመውሰድ ለስኬታማነቱም የሌሎች የአንድነት ኃይሎች ድጋፍና ትብብር የሚሻ መሆኑን በመግለጽ ጥሪውን አስተላልፏል:: ኢሕአፓ ለዚህ ጉዳይ ትኩረት በመስጠት በከፍተኛ ደረጃ የሚንቀሳቀስበት መሆኑን ይገልጻል::

- ➢ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትን መኖር ያመነ ቃሉንም በፖለቲካው መድረክ ያስተዋወቀና ያስተጋባ የመጀመሪያ የፖለቲካ ድርጅት ኢሕአፓ ነው:: የበርካታ ፓርቲዎች መኖርን በማመኑና ለዚያም መከበር በመታገሉ በቡርዥዋ ርዕዮት አቀንቃኝነት ተፈርጆ መደምሰስ ያለበት ነው ተብሎ በወያኔ ተዘልፏል:: በርካታ መግለጫዎችንም አውጥተውበታል:: በፀረ ዴሞክራሲነትም ተወንጅሏል:: የኢሕአፓን የመድበለ ፓርቲ መርህን እንደጦር የሚፈራው ወያኔ መርሁ ተቀባይነት እንዳያገኝ መጠነ ሰፊ ቅስቀሳ ያካሄደበት የነበረ ቢሆንም፣ በወቅቱ ይደግፉት በነበሩት ባዕዳኖች "ያለ ዴሞክራሲ ዕርዳታ አንሰጥም" በሚል ግፊት ሲያረጉበት (ወደመጨረሻ) ተቀበልኩ ቢልም፣ በተግባር በሀገራችን የሰፈነው ግን በመለስ ዜናዊ ቁንጮነት የሚመራ፥ ዘረኛና ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት ሥርዓት ነው::

ስለመድበላዊነት ስናነሳ መርሁ:

1. መሠረታዊ መብቶች ለሰው ክቡርነትና ነፃነት ምንጭ ከመሆናቸው ሌላ መድበላዊነትን የሚያጠናክሩ መሆናቸው፣
2. የፖለቲካው ሂደት ክፍትና ግልጽ መሆኑ፣
3. የሕዝቡን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያሰፉ መሆኑ፣
4. የሥልጣን ክፍፍልና ገደብ በግልጽ የሚንፀባረቅበት መሆኑ
5. አስተዳደሩ ምንጊዜም ጆሮው ለሕዝብ ጥያቄ ክፍት መሆኑ

ላይ የሚገነባ ነው::

ስለሆነም በነፃነትና በዴሞክራሲ መርሆዎች ላይ በሚኖረን ግንዛቤ የሚመሠረተው የመድበላዊነት ጽንሰ ሃሳብ እንደ የሕብረተሰብ ሥርዓት መረዳት ከተቻለ፤ በሕብረተሰቡ ውስጥ በተፎካካሪነት የሚገኙትን የተለያዩ የጥቅም ፍላጎት ዓይነቶችን፥ ሃሳቦችን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው። ዴሞክራሲ እንደመድበላዊ የፍላጎት ግንባታ ሥርዓት ሲታይ የሚያመለክተው በመሠረታዊ መብቶች ላይ የሚመሠረት መሆኑን ነው። በዕውነትም ደግሞ የመሠረታዊ መብቶች ሲጨመቁ የሚሰጡት መድበላዊ ሥርዓትን ነው። የመለስ አገዛዝ ይህንን ተቃርኖ የቆመ ጠላት መሆኑን በገቢር አስመስክሯል። በመሆኑም ዴሞክራሲና መድበላዊነት በጣም የተያያዙ በመሆናቸው፤ ለሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር ስንታገል የአምባገነንነት ተቃራኒ ለሆነው ለመድበለ ዴሞክራሲ (ለመድበለ ፓርቲ) መታገል ማለት በመሆኑ ይህም መሪ መፈክራችን ሆኖ ይቀጥላል። ዴሞክራሲም ከወያኔ የምርጫ ቧልት ሊገኝ እንደማይችል የደም ዋጋ ከፍለን ተምረናል።

ለማጠቃለል፥ እነሆ 37 ሚያዚያዎችን ያስቆጠረው ኢሕአፓ፥ ከላይ በስፋት እንደተዘረዘረው፥ የመነሻ መሠረቶቹ የሆኑትና በየካቲት 66 ከሕዝቡ ጋር አንስቶ የተንቀሳቀሰባቸው ጥያቄዎች ዛሬም ምላሽ አላገኙም። ጭቆናው በተለያየ በከፋ ደረጃ በተለየ መልክ ቀጥሏል። የችግሮቹ ቀጣይነት እስካለና መፍትሄም እስካላገኙም ድረስ፤ ለዚሁ ዋና ተጠያቂ የሆነውን የመለስ አገዛዝ በሁሉም የትግል ስልት ተቋቁሞና ታግሎ ማሸነፉ የግድ እንደሚል ይታያል። ስለዚህም የትግላችን ዒላማ ምን እንደሆነ ከግልጽም ግልጽ ነው። ሕዝብ ይህንኑ ገዥ ቡድን ጠላት ብሎ ከፈረጀው ዓመታት አልፏልና፥ በዚህ ላይ ብዥታን የሚፈጥሩ ሰልፋቸው ከመለስ ጎን እንጂ ከብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ልጨርሶ ሊሆንም አይችልም። አገዛዙን ጠርቦ ማስተካከል የሚለውም ቅዠት፥ አሁንም ሕዝብን ለማደናገር ደፋ ቀና ማለት ብቻ ሳይሆን በገዛ አንገት ላይ የመታነቂያ ገመድ ማጥለቅ ነው። ምርጫው ግልጽ ነው። ትግላችን እንዴት ለሚለው አገዛዙ ራሱ በአፈና፥ በግድያው፥ በስየቱ ለሰላም እምቢተኝነቱን መልስ ሰጥቶበታልና ልዩ ውይይት የሚያሻው አይደለም። የሰፊውን የህብረተሰብ ክፍል በሚያጠናክሩና በሚያስተባብሩ ጥያቄዎች ዙሪያ ማደራጀት፥ አቅጣጫ ማስያዝ ማታገል ብሎም አመራር መስጠት፤ ትግሉ ከማን ጋር የሚለውን የኅብረት ጥያቄ የሚመልስ ነውና፤ ትኩረቱ የሁሉም ወደሕዝቡ ሊሆን እንደሚገባ ጠቋሚ ነው። ከዚህ አንጻር የኢሕአፓ አቋም በተደጋጋሚ ተብራርቷል፤ እናም ከግልጽም ግልጽ ነው።

ትግላችን ይቀጥላል!
ድል የሕዝብ ነው!